# ኤፌ 6፡10-20

"… መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና
ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም
ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ
በክፉዉ ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦር ሁሉ አንሱ ። እንግዲህ ወገባችሁን
በእዉነት ታጥቃችሁ፤ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፤ በሰላም
ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉምላይ
ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉዉን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ
የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሱ፤ የመዳንንም ራስ ቁር ፤
**የመንፈስንም ሰይፍ ያዞ** እርሱም **የእግዚአብሔር ቃል** ነዉ። …."





# የመንፈስ ሰይፍ



1. ሰይፍ

2. የእግዚአብሔር ቃል

3. የቃሉ ኃይል

4. የኛ ድርሻ



# ሰይፍ

- ምንድነዉ?

 - ቀጥ ያለ ወይም ትንሽ የጎበጠ፤ አንድ ወይም ሁለት የተሳለ ጠርዝና እጄታ ያለው መሳሪያ

 - የሞት ወይም የጥፋት መሳሪያ

- ጥቅሙስ?

 ሀ. ጠላትን ለማጥቃት

 ለ. እራስን ለመከላከል



# ሰይፍ

ሰይፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ በስፋት (ከ 400 ጊዜ በላይ) ይጠቀሳል

ዘፍ 3፡ 24

"...አዳምንም አስወጣው፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል **ሰይፍን** በዔድን ገነት ምስራቅ አስቀመጠ ..."

ራዕይ 19፡21

"... የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠዉ ከአፉ በሚወጣው **ሰይፍ** ተገደሉ ወፎችም ከስጋቸው ጠገቡ ..."



# የእግዚአብሔር ቃል

እግዚሐብሔር በተለያየ መንገድ ከሰው ጋር የሚነጋገርበት ነው (ዕብ 1፡1)

1. በራሱ ድምጽ በቀጥታ ለቀድሞ አባቶች
   (1 ነገ 22፤19፣ 1 ሳሙ 9፡27፤ መዝ 85፡ 8)

2. በህልምና በራዕይ ለነብያት (ኢሳ 6፡1፤ ሚክ 1፡11፤ አሞጽ 7፡1)

3. በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሰዎች በጻፉት ( ሆሴዕ 1፡1፤ ኤር 47፡1፤
   ኢሳ 40፡5፤ 2ጢሞ 3፡16 …)

4. በድርጊቱ (በሚያደርጋቸው ተአምሮች) (ዘጸ 9፡5፣ ኢሳ 9፡8፣ ኤር 39፡16፣ …)

5. በልጁ በጌታ ኢየሱስ
   ( ዕብ 1፡1 ፤ ማቴ 17፡5፤ ዮሐ 1፡18፣ ዮሐ 17፡14፣ ዮሐ 20፡21)



# የእግዚአብሔር ቃል

ኤር 15፡16

..... ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ አቤቱ የሰራዊት አምላክ ሆይ በስምህ ተጠር
ቻለሁና ቃልህ ሀሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ

ኢዮብ 23፡ 10-12

... የምሄድበትን መንገድ ያውቃል ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ ...
መንገዱንም ጠብቄአለሁ ፈቀቅም አላልኩም .. የአፉን ቃል በልቤ ሰዉሬዋለሁ

ሮሜ 10፡17

.... እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው



# የእግዚአብሔር ቃል

ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ለሕይወትና ለቅድስና
የሚያስፈልገውን ሁሉ ይሰጣል

መዝ 119፡ 9-11

... ከትእዛዝህ አታርቀኝ አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ

119፡105

....ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው።

ዕዝ 7፡9-10

.... የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው
የዚያን ጊዜም መንገድህ ይከናወንልሃል



# የቃሉ   ኃይል

- ማቴ 4፡1-11

ዲያቢሎስ ጌታ ኢየሱስን  ሲፈትን የተቋቋመውና  ድል ያደረገው በውስጡ ባለው የቃል ሃይል  ነው።

1. ….ድንጋይን ወደ ዳቦ ለዉጥ

….ሰዉ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ …
በሥልጣን ራስን መጥቀም (የግል ፍላጎትን ማርካት)

2. ….   ወድ ታች እራስህን ወርውር ….

….  ጌታን አምላክህን አትፈታተን ተብሎ ተጽፏል ….

የእግዚአብሔርን  ትክክለኛ ድርሻ / ቦታ አለማወቅ

3.
… ወድቀህ ብትሰግድልኝ …..

…. ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል …

ምድራዊዉን ፍላጎት ለማርካት ራስን ማራከስ



# ሰይፍና የእግዚአብሔር ቃል

ኢሳ 49፥2

… ከእናቴ ሆድ ጀምሮ ስሜን አንስቷል አፌንም እንደተሳለ ሰይፍ
አድርጓል

ዕብ 4፡12

“ የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነውና የሚሰራም ሁለትም አፍ ካለዉ ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነዉ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል”



# የቃሉ ኃይል

## 1. ሕያዉ ነው

ዮሐ 6፥63
… እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው ….
ሥራ 7፥38
…. ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ …

## 2. ኃያል ነው

ኤር 23፥29
…. በውኑ ቃሌ እንደ እሳት ድንጋዩንም እንደሚያድቅ መዶሻ አይደለምን?



# የቃሉ ኃይል

3. ይሰራል

ኢሳ 55፡ 10-11
…ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላኩትንም ይፈጽማል እንጂ ወደኔ በከንቱ አይመለስም …

4. ይመረምራል

1ነገ 3፡9 … መልካሙንና ክፉዉንም ይለይ ዘንድ ለባሪያህ አስተዋይ ልቦና ስጠው….



# የዕቃ ጦሩን (የመንፈስ ሰይፉን) እንዴት እናነሳለን?

## 1. ቃሉን በብቃት በማጥናት

2ጢሞ 3፡16-17
.... የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሓፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም
ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል

1ጴጥ 2፡ 1-3
.... አሁን እንድተወለዱ ሕጻናት ተንኮል የሌለብትን የቃልን ወተት ተመኙ ..

## 2. ቃሉ ከኛነታችን ጋር በመንፈስ እንዲዋሃድ በመጸለይ

ኤፌ 6፡ 18

... በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ ....

## 3. እንደ ቃሉ በመኖር

1. በቃሉ ትክክለኛንት በማመን
2. ቃሉ አካሄዳችንን እንዲመራ እራሳችንን በማስገዛት
3. እንደቃሉ ትእዛዝ በመኖር

